ፓኖራማ ቁጥር 53

የትዝብት አድማስ

ህዳር 26 ቀን 2001

<u>የአመኑት ፈረስ ይጥላል በደንደስ</u>

የሰው ልጅ ታሪክን መመዝገብ ከጀመረበት አንስቶ አሁን እስከደረሰበት የሥልጣኔ ደረጃ ያለውን ሁኔታ ዕድሜውና አቅሙ እስከፈቀደለት ድረስ መታዘቡና መገንዘቡ የነበረና ያለም ነው:: ግንዛቤውና ትዝብቱ ግን ከሰው ሰው ይለያያል:: ዕምነትን የሚያጎድል፥ ምሥጢርን የሚዘከዝክ፥ እንዳስቀመጡት የማይገኝ፥ ወዳጁን የሚጎዳ፥ ባልንጀራውን የሚከዳ፥ በያንዳንዱ ኅብረተሰብና በመቸውም የጊዜ ቀመር ሲፈፀም የነበረ ክስተት ነው:: ይህ ክስተት በግለሰብ፥ በቤተሰብ፥በኅብረተሰብ፥ በድርጅት፥በሀገርና በመንግሥትም በኩል በየዕርከኑና በየደረጃው ሲፈፀም ቆይቷል::ሕብረተስብና ዓለም አብረው እስከተጓዙ ድረስም ይህ ክስተት የሚቀጥል ነው የሚሆነው:: በተለይ የዓለም ሕዝብ ቁጥር እየጨመረ፥የሚኖርባት ምድር እየተጨናነቀች፥ለሰው ልጅ አስፈላጊ የሆኑት አቅርቦቶች እያጠሩ ሲሄዱ፥ኢኮኖሚው እየወደቀ፥የፋይናንስ ምንጭ እየነጠፈ ለኢንዱስትሪዎች የሚሆነው ጥሬ ሀብት ሲያከትም፥የነዳጅ ጉድጓዶች ሲደርቁ ኀያሉ ደካማውን በበለጠ እያጠቃው ሲሄድ ለመኖር ሲባል አንዱ ሌላውን እየከዳውና እየካደው መሄዱ የማይቀር ነው::ይህ ክስተት በተለየ መልኩ በስፋት ሊፈፀም የሚችለው፥ በሀገሮችና በመንግሥታት መካከል እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታ ነው:: በተለየማ ታላላቅና ሰልጥነዋል በሚባልላቸው ሀገሮችና መንግሥታት ዘንድ፥ለማመን በሚያስቸግር ፍጥነትና ስፋት፥ እየከዱ አጋልጦ መሄዱ የማይቀር ነገር ነው::

በመሠረቱ፥ በመንግሥታት መካከል ቋሚ ወዳጅና ጠላት የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም ስለሚባል፥ ትኩረታቸውና ዘላቂ ዕቅዳቸው የሚያነጣጥረው በዘላቂ ጥቅማቸው ላይ ብቻ ስለሚሆን፥ ወዳጅም ሆነ የትብብር አለኝታ የሚባል ነገር ሊኖራቸው አይችልም::ባጭሩ፥ለዘላቂ ጥቅማቸው እንጅ ለአፍለኛ ወዳጆቻው ቅንጣት ያህል ደንታ አይሰጡም:: ቋሚ መመሪያቸውና የፖለቲካ አሰራራቸው በእከከኝ -ልከክህ ላይ በተመሠረተ የጥሎ ማለፍ አካሄድና ፍርጠጣ ላይ ይሆናል:: ይህንን ጉዳይ ወደ ከፋ መልኩ ሲያሸጋግሩት ደግሞ፥ የፖለቲካ ሳይንሳቸውን የሚያነጣጥሩት፥ጊዜያዊ አገልጋዮቻቸውን እየተጠቀሙ፥ጊዚያዊ ጠላቶቻቸውን በመጉዳት ነው::ይህ ሁኔታ በዓለም አቀፍ የየሀገሮች ዝምድናም ይሁን የዲፕሎማቲክ አካሄድ የተለመደ መሆኑ ሁሉም ያውቀዋል:: ምን ጊዜም ቢሆን በዚህ ጨዋታ ተጠቃሚ ሲሆን የነበረው "ኀይል ትክክል ነው" የሚለውን ካርታ ጨብጦ የተገኘው ብቻ ነው:: ለዚህ ሀቅ እንደ ህያው ምስክር የሚጠቀሰው በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት

በፀጥታው ምክር ቤት ውስጥ ድምፅን በድምፅ የመሻር ኃይል( የቬቶ ኃይል) ያላቸው አምስት ሀገሮች ብቻ ናቸው። የመላው ዓለም ሕዝቦች በነኝህ አምስት ሀገሮች ብቻ የመኖርና ያለመኖር ዕድላቸው ይወሰንላቸዋል/ ይወሰንባቸዋል። ለዚህ ተጨባጭ ማስረጃ የሚሆነው፥ በአንድ ኀያል መንግሥት በኩል በኢራቅ ላይ የተካሄደው ወረራ ነው። ከእነኝህ አንዱን ወይም ሌላውን ያመነ/ያላመነ በደንደሱ የመውደቅ ወይም ያለ መውደቅ ዕድሉን ያገኛል።

የዓለም ሕዝቦች የመኖር/ ያለመኖር ዕድላቸው በነኝህ ኀያላን መንግሥታት ስር በመሆኑ ሁላቸውም የተሟላ የፖለቲካ ፥የምጣኔ ሀብትና የማኅበራዊ ኑሮ ነፃነታቸው የተረጋገጠ ነው ማለት አይቻልም። ማነኛቸውም ሀገሮች የዛሬይቱ ዓለም የምትተዳደርበትን ሥርዓት በሚገባ ተረድተው ለመኖር ብቻ ሲሉ በሚያደርጉት መፍጨርጨር፥የሚያምኑትን ፈረስ ጥቅም ማስጠበቅ እስካልቻሉ ድረስ፥ያ የተማመኑበት ኀይል በደንደሳቸው ጥሎ ሌላ ገለባ አቅራቢ እንደሚፈልግ የተሰወረ አይደለም። ኀያላኑ በሚጋልቡት ፈረስ ኮርቻ በስተኋላ ተፈናጥጠው ሲንከራተቱ የሚቆዩ ጋሻጃግሬዎች ያፈናጠጧቸውን ጌቶቻቸውን ጥቅም ካላስጠበቁላቸው፥በአፍ ጢማቸው ተደፍተው እንደሚወድቁ በርካታ ማስረጃዎችን መጥቀስ ይቻላል። ይህ በግል ጥቅምና በሃብት ሽሚያ ላይ የተመሠረተው የዓለም አቀፍ ዘማዊ ዲፕሎማሲ ይትበሃል፥ የተፈራረሙበትን ውል በማፍረስና የተስማሙበትንም ቃል ኪዳን በመካድ፥የተማመኑባቸውን ሰይፈ-ጃግሬዎች በሚያስደንቅ ፍጥነት ሲከዷቸው፥“ያመኑት ፈረስ ጣለ በደንደስ” የሚባለው ተረት ቢተረክባቸው የሚያስገርም አይሆንም።

በቅርቡ አዲስ ለተመረጠው ሰው ሥልጣኑን የሚያስረክበው የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ቡሽ፥ በሀገራችን በኢትዮጵያ ላይ ተዘርዝሮ የማያልቀውን ግፍና በደል መፈፀሙና ማስፈፀሙ የኢትዮጵያ ሕዝብ በከፍተኛ ሀዘንና ትካዜ የሚያስታውሰው ነው። እንዲያው በደፈናው ከአሁን በፊት የነበሩት የአሜሪካ መንግሥት ባለሥልጣናት ከወያኔ ጋር በመተባበር ሀገራችንን ከመኖር ወደ አለ መኖር ደረጃ ለማድረስ ከፍተኛውን ሚና ተጫውተዋል ብሎ በመደምደም ለጊዜው ማለፉ ይመረጣል። ምርጫችን ይህም ባይሆን እንኳ፥ለጊዜወው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁኔታውን ለመለወጥ የሚያስችለው ኃይልና ጉልበት እንደሌለን ይገነዘባል። ይህ ማለት ግን ለረዥም ጊዜ የወያኔ መጫወቻ ሆኖ ይቀራል ማለት አይደለም። ይዋልም ይደር፥ ኢትዮጵያ ሀገራችን፥የዴሞክራሲ ሥርዓት መስርታ የራሷን የፖለቲካ ፥ የምጣኔ ሃብትና የነፃነት ልዕልናዋን እንደምታስከብር ማንም ሊጠራጠር አይችልም።

ሀገራችንን አስመልክቶ፥በአዲሱ ተመራጭ ላይ የተለያዩ አስተያየቶች ሲሰነዘሩ ይሰማል።አብዛኛዎቹ አስተያየቶች የተመሠረቱት፥ከሞላ ጎደልም ቢሆን፥ “ዘመድ የሌለው ሰው ወደ ሚስቱ ዘመድ ይጠጋል” በሚለው አነጋገር ላይ ይመስላል።መለስ ዜናዊ ከቡሽ አስተዳደር በኩል ሲለገሰው የቆየው ሁለንተናዊ ድጋፍ አደጋ ላይ ይወድቅብኛል ብሎ ስለሰጋ፥አሜሪካ ሀገር የሚኖሩትን የወያኔ ደጋፊዎች ሁሉ፥ ኦባማን እንዳይመርጡና ድምፃቸውን ለበላይ ጠባቂያቸው

ለቡሽ ፓርቲ እንዲሰጡ ከፍተኛ ቅስቀሳና ተማፅንዖ ቢያደርግም፥ የተመኘው ሳይሆንለት ቀርቷል። በአሜሪካ ሕዝብ ድምፅ ውሳኔ  የቡሽን ፖሊሲ ለማስቀጠል የተደረገው ጥረት ሳይሳካ በመቅረቱ፥ የመለስ ዜናዊ የጡት አባቶች ያመኑት ፈረስ በደንደስ እንደሚጥል ሁሉ፥ መለስ ዜናዊን በዘለዓለማዊ መልኩ ድጋፋቸውን ሊለግሱለት በሚያስችላቸው ሁኔታ እንደማይቀጥሉለት ተረድቶታል። ምናልባት አዲሱ የኦባማ አስተዳደር መለስን በአዲስ ልጓም ለመጋለብ እስካላስፈለገው ድረስ አሜሪካኖች ወያኔዎቹን እንደ አሮጌ ቁና እንደሚወረዉሯቸው ለማንም የተደበቀ አይሆንም። ይህ እንዳይሆን ደግሞ፥ ወያኔዎቹ አዲስ ጥርስ  በማብቀልና አዲስ ኮርቻም በማመቻቸት አገልግሎታቸውንና ታመኝነታቸውን ለመግለፅ  ሙከራ ማድረጋቸውን ይተውታል ለማለት አይቻልም።አዲስ የሚመጣው የኦባማ አስተዳደር፥ ጥገናዊ በሆነ መልኩ፥ምናልባት አንዳንድ የይዘት ሳይሆን የቅርፅ ለውጥ ለማድረግ ቢከጅልም፥ ከአሜሪካ መሠረታዊ ጥቅም አኳያ የመለስ አገልጋይነት ይጠቅመኛል በሎ ከገመተ፤መለስ ዜናዊ አዲስ ቅጥረኛ ለመሆን እራሱን አዘጋጅቶ አይቀርብም ብሎ የሚገምት የለም። እንዲያውም፥"ሎሌ ባፍላው፥ የአህያ መኸገር ይከላል" እንደሚባለው፥ ለአዲሱ የበላይ ጠባቂው ማነኛውንም ሁሉ አድርጎ ለአገልግሎት እንደሚቀርብ  ማንም ኢትዮጵያዊ በትክክል የሚገምተው ሀቅ ነው። አዲሱ የኦባማ አስተዳደር የመጀመሪያው ኃላፊነቱ፥ ተጠያቂነቱና ተልዕኮው፥ የአሜሪካንን መሠረታዊና ዋና ጥቅም መጠበቅና ማስጠበቅ ስለሚሆን፥ለውጥ ይመጣል ከተባለም፥ የፖሊሲ ለውጥ ሳይሆን፥ ለፖሊሲው  ማስፈፀሚያ ጠቃሚ ናቸው የሚባሉት የአገልጋዮች ለውጥ ነው። እነ መለስ ዜናዊ ደግሞ በመሠረተ ባኅርያቸው ሳይለወጡ፥ ለአዲሱ ጌታ አገልግሎት የሚያበቃቸውን  የእስስት ባኅርይ ለውጥ አድርገው ለመቅረብ ልዩ ችሎታ ያላቸው ፍጥረቶች ናቸው።ሲያምኑት የነበረው የቡሽ አስተዳደርማ እንደ አገዳ መጥጦ ትቷቸው እየሄደ ነው።

ምንም ይሁን ማን ቢመጣ- ቢሄድ፥ ብሎም ሁኔታዎች ቢለወጡ- ቢለዋወጡ በኢትዮጵያ ዘላቂ ጥቅም መደራደር  አይቻልም ብሎ ከጥንት ከጧቱ ቆርጦ በመነሳት የሚታገለው ኀይል ብቻ ነው ፥ኢትዮጵያን የሚጠብቃት። ይህ ኢትዮጵያዊ ኀይል ደግሞ፥ በየወቅቱ እንደ እስስት እየተለዋወጠ በኢትዮጵያ ሕዝብ ጀርባ የመደራደር ባኅርይም ሆነ ተልዕኮ የለውም።ይህንን የማይበረዝ ብሎም፥እንደ ብረት የጠነከረ አቋም አንግቦ ለመታገል፥ ከሁሉ በፊት፥ ኢትዮጵያዊ ወኔ እንዲኖር ያስፈልጋል። ይህ ወኔ ደግሞ ለሁሉም የሚታደለው ባኅርይ ሊሆን አይችልም። የአንድን ሀገር መሠረታዊ ጥቅምና ኀልውና ለባዕድ አሳልፎ በመስጠት የሚመጣው ማነኛውም ዓይነት "ጥቅም" በአፍንጫችን ይውጣ ብለው የሚታገሉ ኀይሎች፥ ከዚህ አቋም ከመድረሳቸው በፊት የሀገራቸውንና የሕዝባቸውን ፍቅር መሠረት አድርገው መነሳት አለባቸው። ወያኔዎቹ ደግሞ የኢትዮጵያንና የሕዝቦቿን  ጥቅም አሸቀንጥረው የጣሉ ጠባብ ብሄረተኞች ናቸው። የሀገራችውን ሕዝብ ፍቅርና ተአመኔታ ሳያገኙ በመቅረታቸው፥ የባዕድን ወዳጅነትና ታማኝነትን ለማግኘት በመጣራቸው፥ በኩርናቸውን በጭብጥ ምስር የለወጡ ሆነዋል። የባዕድ ታማኝነት ደግሞ ወረቱ ሲያልቅ እንደ አመኑት ፈረስ በደንደስ  እንደሚጥል የታሪክ ሀቅ ነው።